# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት፣ ማሽነሪዎችንና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 38/2013

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓታት ላይ በሚታየው ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅና አደጋ እንዲሁም የከባቢ አየር ብክለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች እንዲሁም የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት እና የውበትና መናፈሻ ቦታዎችን ውሃ የሚያጠጡ ተሽከርካሪዎች አስተዋጽኦ የጎላ በመሆኑና ይህንን መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ እና የእነዚህን ተሽከርካሪዎች ወደ ከተማዋ መግባት የሚችሉበትንና በከተማው ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን ሰዓት በመወሰን ችግሮቹን መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በሰዓት መገደቡ ፍሰቱን ከማሳለጡም በተጨማሪ በዚህ መመሪያ እንቅስቃሴያቸው የተወሰነላቸው ተሽከርካሪዎችም አገልግሎታቸውን በተቀላጠፈ ሁኔታና የሎጂስቲክስ ወጪን በሚቀንስ መልኩ ማከናወን እንዲችሉ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤

በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ፊደል ተራ (ረ) እና (ሰ) ድንጋጌዎች መሠረት የህዝብን ደህንነት የሚጎዱ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ ማገድ እንዲሁም ከተሞቹ የትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን እንዲችሉ የፌዴራል የትራንስፖርት ባለስልጣን የውክልና ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰጠው በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 3(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት፣ ማሽነሪዎችን እና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 38/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

2.1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

2.2. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

2.3. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፤

2.4. **"መንገድ"** ማለት ተሽከርካሪዎችና እግረኞች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኝ መንገድ ወይም መተላለፊያ ነው፤

2.5. **“ትራፊክ”** ማለት በማናቸውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኝ መንገድ ላይ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚነዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፤

2.6. **“የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ”** ማለት 2.5 ቶን (25 ኩንታል) እና ከዛ በላይ የሆነ የመጫን አቅም ያለው በከተማው መንገድ ላይ የሚሄድ ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራ ባለሞተር ቀላል ተሽከርካሪ፣ ከባድ ተሽከርካሪ፤ ባለተሳቢ ወይም ተሳቢ የሌለው ተሽከርካሪ ሲሆን ቀላል የጭነት ተሽከርካሪ እና ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ ተብሎ ይከፈላል፤

2.7. **“መንቀሳቀሻ ፈቃድ”** ማለት በዚህ መመሪያ ወደ ከተማ ለመግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ በተከለከለ ሰዓት ወደ ከተማ እንዲገቡ ወይም እንዲንቀሳቀሱ ለሚፈቀድላቸው የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በኤጀንሲው የሚሰጥ ፈቃድ ሲሆን መደበኛ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ እና ልዩ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ተብሎ ይከፈላል፤

2.8. **“መደበኛ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ”** ማለት ከሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጭ ከቀኑ 4:00 እስከ ቀኑ 10:00 ወደ ከተማ ለመግባትና በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ በኤጀንሲው የሚሰጥ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ዓይነት ነው፤

2.9. **“ልዩ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ“** ማለት በሥራ መግቢና መውጫ ሰዓት ከማለዳ 12:30 እስከ ጠዋቱ 4:00 እንዲሁም ከቀኑ 10:00 እስከ ምሽቱ 2:00 ሰዓት ወደ ከተማ ውስጥ ለመግባትና በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ ለቀላል የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካዎች በኤጀንሲው የሚሰጥ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ዓይነት ነው፤

2.10. **“የፈቃድ ምልክት”** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ወደ ከተማ ለመግባትና በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ በኤጀንሲው ፈቃድ ስለመሰጠቱ የሚያመለክት መረጃ የያዘና በተሽከርካሪው የተፈቀደ ቦታ ላይ የሚለጠፍ ወይም በብሎን የሚታሰር ስሌዳ ነው፤

2.11. **“የበዓላት ቀናት”** ማለት አግባብ ባለው ሕግ መደበኛ ሥራ እንዳይሰራባቸው የተለዩ ሐይማኖታዊና ብሔራዊ በዓላት ናቸው፤

2.12. **“የተሽከርካሪ መከታተያ ስርዓት”** ማለት የጂፒኤስ ሳተላይቶችን በመጠቀም የአንድን ተሽከርካሪ መረጃ በማስተላለፍ የተሽከርካሪውን እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው፤

2.13. **“ቀላል የጭነት ተሽከርካሪ”** ማለት የመጫን አቅማቸው ከ25 ኩንታል እስከ 35 ኩንታል ወይም ከ2.5 እስከ 3.5 ቶን የሆኑ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤

2.14. **“ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ”** ማለት የመጫን አቅማቸው ከ35 ኩንታል ወይም ከ3.5 ቶን በላይ የሆኑ ባለተሳቢና ተሳቢ የሌላቸው የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤

2.15. **“የኮንስትራክሽን ማሽነሪ”** ማለት የተለያዩ የኮንስትራክሽን ስራዎችን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውሉ ማናቸውም ባለብረትም ሆነ ባለጎማ ማሽነሪዎች ማለት ነው፤

2.16. **“የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎች”** ማለት በከተማዋ የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ የማንሳት አገልግሎት የሚሰጡ በደበኛና ልዩ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤

2.17. **“የውብትና መናፈሻ ተሽከረካሪዎች”** ማለት በከተማዋ የመንገድ ዳርና የመንገድ ማካፈያ እንዲሁም ከመንገድ ውጭ በሚገኙ ተክሎችና የመናፈሻ ቦታዎችን ውሃ የማጠጣት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤

2.18. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ክልል በሚገቡና በከተማ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ እንዲሁም ከተማዋን አቋርጠው በሚያልፉ የመጫን አቅማቸው 2.5 ቶን ወይም 25 ኩንታል እና ከዛ በላይ የመጫን አቅም ያላቸው የተለያዩ የፈሳሽና የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪዎች፣ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች እንዲሁም በከተማው ውስጥ የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ የማንሳት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች እና በከተማው ውስጥ የውበትና መናፈሻ ቦታዎችን ውሃ የማጠጣት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከረካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ሰዓት ገደብ እና ስለ ፈቃድ

4. የሰዓት ገደብ ስለመወሰን

4.1. ማናቸውም ቀላል የጭነት ተሽከርካሪዎች ከጠዋቱ 12፡30 እስከ 4፡00 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 10፡00 እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ወደ ከተማ ውስጥ መግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ እንዲሁም ጭነት ማራገፍም ሆነ መጫን የተከለከለ ነው፤

4.2. ማናቸውም ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች ከማለዳው 12፡30 እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ወደ ከተማ መግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ እንዲሁም የጭነት መጫንና ማውረድ ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው፤

4.3. ማናቸውም ባለብረትም ሆነ ባለጎማ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ወደ ከተማ ውስጥ መግባትም ሆነ መንቀሳቀስ እንዲሁም ጭነት መጫንና ማራገፍ የሚችሉት ከምሽቱ 2፡00 እስከ ማለዳ 12፡30 ሰዓት ብቻ ይሆናል፤

4.4. ማናቸውም በከተማው ውስጥ የፈሳሽ ቆሻሻ የማንሳት አገልግሎት የሚሰጡ ልዩ ተሽከርካሪዎች በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ የሚችሉት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ብቻ ይሆናል፤

4.5. ማናቸውም የደረቅ ቆሻሻ የማንሳት እና የውበትና መናፈሻ ቦታዎችን ውሃ የማጠጣት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከጠዋቱ 12፡30 እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት በከተማው ውስጥ መንቀሳቀስም ሆነ ውሃ የማጠጣት ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው፤

4.6. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4.1 እስከ 4.5) መሠረት ወደ ከተማ መግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ የተከለከለ የጭነት ተሽከርካሪ ወደ ከተማው ለመግባት በእንቅስቃሴ ላይ እያለ የሰዓት ገደቡ ቢደርስበት በከተማዋ መግቢያ በሮች ላይ በሚዘጋጅ ቦታ ላይ ወይም ከዋና መንገድ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ ላይ የአካባቢውን የትራፊክ እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ በመቆም የሰዓት ገደቡ እስኪያልፍ መጠበቅ አለበት፤

4.7. ማንኛውም የጭነት ተሽከርካሪ በከተማ ውስጥ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ በዚህ መመሪያ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ቢደርስበት የአካባቢውን የትራፊክ እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ የመንገድ ጠርዝ በመያዝ ወይም ከዋና መንገድ ውጭ በመውጣት መቆም ይጠበቅበታል፤

4.8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4.1 እስከ 4.5) ከተደነገገው ሰዓት ውጭ እንዲሁም እሁድ እና የበአል ቀናት ማናቸውም የጭነት ተሽከርካሪዎች ያለምንም የመንቀሳቀሻ ፈቃድ በየትኛውም ሰዓት ወደ ከተማ መግባትም ሆነ መንቀሳቀስ እንዲሁም ጭነት የመጫንና የማራገፍ ተግባር የትራፊክ ህግ ማክናወን ይችላሉ፡፡

## 5. የሠዓት ገደብ የማይመለከታቸው ተሽከርካሪዎች

5.1. ከዚህ በታች የተገለፁት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው በማንኛውም ሰዓት ወደ ከተማ መግባትም ሆነ መንቀሳቀስ ይችላሉ፤

ሀ. የሀገር መከላከያ እና ሌሎች የፀጥታ ስራዎችን የሚያከናውኑ ከባድና ቀላል የጭነት ተሽከርካሪዎች፤

ለ. በህግ መሠረት የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ተብለው የተለዩ የድንገተኛ አደጋ የሚሰሩ ቀላልና ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች፤

ሐ. በከተማ ውስጥ በመንገድ ላይ ተበላሽተው የቆሙ ወይም በአደጋ ምክኒያት መንገድ ዘግተው ያሉ ተሽከርካሪዎችን የማንሳት አገልግሎት ለመስጠት የሚንቀሳቀሱ ሆነው ለዚህ ተግባር እየተንቀሳቀሱ ስለመሆኑ በኤጀንሲው የተሰጠ ማረጋገጫ የያዙ ከሬኖችንና ተሽከርካሪዎችን የሚጎትቱ ተሽከርካሪዎች፤

5.2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው ወደ ከተማ የሚገቡ እና በከተማ ውስጥ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ የጭነት እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ዓይነት ሊወስን ይችላል፡፡

## 6. ስለመንቀሳቀሻ ፈቃድ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ (4) መሠረት ወደ ከተማ እንዳይገቡም ሆነ እንዳይንቀሳቀሱ የተከለከሉ የጭነትና ሌሎች ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ምክኒያቶች በተከለከለው የሰዓት ገደብ ውስጥ መንቀሳቀስ የግድ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ አስቀድሞ ከኤጀንሲው በሚሰጥ የተለያየ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ዓይነት ወደ ከተማ እንዲገቡም ሆነ እንዲንቀሳቀሱ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም የመንቀሳቀሻ ፈቃዱ የሚሰጣቸው ተሽከርካሪዎች በአንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ (4.3) እስከ ንዑስ አንቀጽ (4.5) ያሉትን አያካትትም፡፡

## 7. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ዓይነቶች

7.1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ (4) ንዑስ አንቀጽ (4.1 እና 4.2) ድንጋጌዎች መሠረት በተከለከሉ ሰዓታት ወደ ከተማ ለመግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ እንዲሁም የጭነት መጫን ወይም ማውረድ ተግባር ለማከናወን የሚሰጡ የመንቀሳቀሻ የፈቃድ ዓይነቶ፤

ሀ. መደበኛ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ እና

ለ. ልዩ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ናቸው፡፡

## 8. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ስለሚሰጣቸው የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፤

8.1. ማናቸውም ከባድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መደበኛ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ሆኖም በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (4.3 እስከ 4.5) ያሉትን አያካትትም፡፡

ማናቸውም ቀላል የጭነት ተሽከርካዎች ልዩ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል:: ሆኖም በአንቀጽ 4 ንዑስ

8.2. አንቀጽ (4.3 እስከ 4.5) ያሉትን አያካትትም::

አደጋን ለመከላከል እንዲያስችል ኤጀንሲው የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ለሚሰጣቸው ተሽከርካሪዎች በከተማው

8.3. የፍጥነት ወሰን መመሪያ መሠረት የተለየ የፍጥነት ወሰን ሊወስን ይችላል፤ ይህን የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ያገኙ

ተሽከርካሪዎችም ኤጀንሲው በተለየ ሁኔታ የሚወስነውን የፍጥነት ወሰን የማክበር ግዴታ አለባቸው::

## 9. የመንቀሳቀሻ ፍቃድ ሊጠይቁ የሚችሉ አካላት፤

9.1. በዚህ መመሪያ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው የተሽከርካሪው ባለቤት፣ ወኪል ወይም በሌሎች ህጋዊ ውሎች መሰረት የመጠቀም መብት የተሰጠው አካል ነው::

9.2. በዚህ መመሪያ መሠረት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የማግኘት መብት ያለው የጭነት ተሽከርካሪ ኤጀንሲው ለዚህ ዓላማ በሚያዘጋጀው ቦታ ጥያቄውን በማቅረብ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል::

## 10. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ሰነዶችና ስለሚበረታቱ ሁኔታዎች

10.1. ፈቃዱን ለማግኘት መቅረብ ስለሚገባው ሰነዶች፤

ሀ. የአመልካቹ ወይም የተወካይ መታወቂያ ወይም የውክልና ደብዳቤ፣

ለ. ማመልከቻ ደብዳቤ ወይም ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ፣

ሐ. ሊብሬ ኮፒ፣

መ. የታደሰ ንግድ ፈቃድ ወይም ሕጋዊ የሰውነት ማረጋገጫ እና

ሠ. ተሽከርካሪውን ለመጠቀም የተደረገ ውል (አስፈላጊ ሲሆን)

10.2. ማበረታቻ

ሀ. በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ የማግኘት መብት ያለው የጭነት ተሽከርካሪ ፈቃዱን ለመጠየቅ ሲመጣ ፈቃድ በሚጠየቅለት ተሽከርካሪ ላይ በራሱ ወጪ ጂፒኤስ የተሽከርካሪ መከታተያ ስርዓት እንዲያስገጥም ይበረታታል::

የተሽከርካሪ መከታተያ ስርዓት ያስገጠመ የተሽከርካሪ

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት ጂፒኤስ የተሽከርካሪ መከታተያ ስርዓት ያስገጠመ የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ተወካይ ያስገጠመውን ስርዓት ለኤጀንሲው ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ የመንቀሳቀሻ

ፈቃዱን ከወሰደ ጊዜ ጀምሮ ፈቃዱ እስኪያበቃ ድረስ ክፍት ማድረግ ይኖርበታል::

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የተገጠመው ጂ.ፒ.ኤስ. የተሽከርካሪ መከታተያ ስርዓት ቢበላሽ ፈቃድ ያገኘው አካል ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤ ማስጠገንና አገልግሎቱ ወዲያውኑ እንዲጀምር ማድረግ ይኖርበታል::

መ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ (ሀ) ንዑስ አንቀጽ መሠረት የተሽከርካሪ መከታተያ ሥርዓት ያስገጠሙና ለኤጀንሲው ክፍት ያደረጉ ፈቃድ ጠያቂዎች በአንቀፅ 12 ከተቀመጠው የክፍያ መጠን የ75 በመቶ ቅናሽ ይደረግላቸዋል::

## 11. ስለመንቀሳቀሻ ፈቃድ ምልክት

11.1. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ምልክቱ የሚለጠፍበት ሰሌዳ ከላሜራ የሚሰራ ሆኖ መልዕክቶቹ በቀላሉ ሊበላሽ በማይችልና አንጸባራቂ በሆነ ተለጣፊ (ስቲከር) የተሰራ ይሆናል።

11.2. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ምልክቱ ላይ የሚጻፉ መልዕክቶችና ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ. የፈቃድ ዓይነት

ለ. የተሽከርካሪው የሰሌዳ ቁጥር

ሐ. ፈቃዱ የሚያበቃበት ቀን

መ. የኤጀንሲው ማሕተም

# ክፍል አራት

# የመንቀሳቀሻ ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ስለመወሰን

## 12. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ ተመን

12.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ (7) (ሀ) እና (ለ) መሠረት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የሚጠይቅ የጭነት ተሽከርካሪ

ሀ. መደበኛ ፈቃድ ለማግኘት አንድ ተሽከርካሪ በቀን 500 ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፤

ለ. ልዩ ፈቃድ ለማግኘት አንድ ተሽከርካሪ በቀን 1000 ብር የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፤

12.2. አንድ የጭነት ተሽከርካሪ በአንድ ጊዜ እስከ ሁለት ወር የሚያገለግል የመንቀሳቀሻ ፈቃድ መውሰድ ይችላል።

12.3. ፈቃድ የሚለጠፍበትን ሰሌዳ ኤጀንሲው አሰርቶ የሚያቀርብ ሲሆን ፈቃድ ጠያቂው አካል ውል በመዋዋል ይወስዳል።

12.4. የመንቀሳቀሻ ፍቃድ ለማደስ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከላይ የተገለፁትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላትና ክፍያዎችን በመፈፀም ፈቃዱን ሊታደስለት ይችላል።

# ክፍል አምስት

# የጭነት ተሽከርካሪ የመንቀሳቀሻ ፍቃድ አጠቃቀምን ስለመወሰን

## 13. የፈቃድ አያያዝ

13.1. ማንኛውም በተከለከለው ሰዓት ወደ ከተማ ለመግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ ፈቃድ የወሰደ የጭነት ተሽከርካሪ ፈቃዱን እንዲለጠፍበት በተወሰነው የተሽከርካሪው አካል ላይ በግልፅ ለጥፎ መገኘት አለበት።

13.2. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ምልክቱ የተሰረዘ ወይም የተበላሸ ከሆነ ጥቅም ላይ አይውልም።

13.3. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ምልክቱ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቢበላሽ ወይም ቢጠፋ ለኤጀንሲው በማሳወቅ ፈቃዱን በድጋሚ ማግኘት ይቻላል።

13.4. በተለያዩ ምክንያቶች የመንቀሳቀሻ ፈቃዱ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ሰው አስተዳደራዊ ወጪዎችን በመሸፈን ፈቃዱን በድጋሚ ማግኘት ይችላል፤

13.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (13.4) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንቀሳቀሻ ፈቃዱ ከሁለት ጊዜ በላይ ቢበላሸበት ወይም ቢጠፋበት የነበረው ቀሪ የፈቃድ ቀናት ተሰርዞ እንደ አዲስ ፈቃድ ያወጣል፡፡

## 14. የኤጀንሲው ሃላፊነትና ተግባር

14.1. መመሪያውን በተለያዩ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ፤

14.2. በየከተማው መግቢያ ላይ የጊዜ ገደቡን በተመለከተ መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን የማስቀመጥ፤

14.3. በዚህ መመሪያ መሠረት ልዩ ፈቃድ ለሚሰጣቸው ተሽከርካሪዎች የፈቃድ መውሰጃ ቦታዎችን በማመቻቸት ፈቃድ መስጠትና ማደስ፤

14.4. ለመመሪያው ተግባራዊነት ተገቢውን ቁጥጥርና ደጋፍ ማድረግ፤

## 15. የተከለከሉ ተግባራት

15.1. የመንቀሳቀሻ ፈቃድን ከተፈቀደለት ተሽከርካሪ ውጭ አገልግሎት ላይ እንዲውል አሳልፎ መስጠት ክልክል ነው፤

15.2. የመንቀሳቀሻ ፈቃድን ከተፈቀደለት የሰዓት ክልል ውጭ መጠቀም የተከለከለ ነው፤

15.3. የጭነት ተሽከርካሪ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሰነድን ማስረዝ፣ መደለዝ ወይም አስመስሎ መስራት ክልክል ነው፤

15.4. የፈቃድ ጊዜ ያለፈበት የጭነት ተሽከርካሪ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ማጠቀም የተከለከለ ነው፤

15.5. ማናቸውም በዚህ መመሪያ መሠረት ወደ ከተማ ለመግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ ፈቃድ የተሰጠው የጭነት ተሽከርካሪ ኤጀንሲው አዘጋጅቶ ከሚሰጠው ፈቃድና በተሽከርካሪው እንዲለጥፍ ከወሰነው የተሽከርካሪው አካል ውጭ መለጠፍ የተከለከለ ነው፤

15.6. ለሌላ ተሽከርካሪ የተሰጠን የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ማጠቀም፤

15.7. ማናቸውም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8.1) እና (8.2) መሠረት ወደ ከተማ ለመግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የተሰጠው ተሽከርካሪ ከተፈቀደለት ዓላማ ውጭ መንቀሳቀስ አይፈቀድለትም፡፡

## 16. ስለቅጣት

ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶችና የቅጣት ዓይነትና መጠን

ሀ. የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሳያወጡ ወይም ሳይዙ በተከለከለ ሰዓት ወደ ከተማ መግባትና በከተማ ውስጥ መንቀሳስ እንዲሁም በዋና መንገድ ላይ የጭነት መጫንና ማውረድ ተግባር መፈፀም፤

ለ. ጊዜው ያለፈበት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ ወደ ከተማ መግባት ወይም በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ፤

ሐ. የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፤

መ. የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም አስመስሎ የተሰራ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ መገኘት እና መጠቀም፤

ሠ. የመንቀሳቀሻ ፈቃድን ከተፈቀደለት የሰዓት ክልል ውጭ መጠቀም፤

ረ. የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ከሁለት ጊዜ በላይ መጣል ወይም ማበላሸት፤

ሰ. ለሌላ ተሽከርካሪ የተሰጠ የመንቀሳቀሻ ፈቃድን እንደራስ አስመስሎ መጠቀም፤

ሰንጠረዥ ፣ የቅጣት ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የጥፋቱ ድግግሞሽና የቅጣት መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ጊዜ | ለሁለተኛ ጊዜ | ከሁለት ጊዜ በላይ |
| 1 | የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሳያወጡ ወይም ሳይዙ በተከለከለ ሰዓት ወደ ከተማ መግባትና በከተማ ውስጥ መንቀሳስ እንዲሁም በዋና መንገድ ላይ የጭነት መጫንና ማውረድ ተግባር መፈፀም | 1,000.- | 2,000.- | 3,000.- ብር ተቀጥቶ የአሽከርካሪው መንጃ ፈቃድ ለ1 ወር ይታገዳል፡፡ |
| 2 | ጊዜው ያለፈበት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ ወደ ከተማ መግባት ወይም በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ | 500.- | 1,000.- | 4,000.- ብር ተቀጥቶ የአሽከርካሪው መንጃ ፈቃድ ለ2 ወር ይታገዳል፡፡ |
| 3 | የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ከተፈቀደለት የሰዓት ክልል ውጭ መጠቀም | 500.- | 1,000.- | 2,000.- ብር ተቀጥቶ የአሽከርካሪው መንጃ ፈቃድ ለ1 ወር ይታገዳል፡፡ |
| 5 | የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም አስመስሎ የተሰራ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ መገኘት እና መጠቀም፣ እንዲሁም የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፣ እና ለሌላ ተሽከርካሪ የጠሰጠ ፈቃድን እንደራስ አስመስሎ መጠቀም | 6,000.- ብር ተቀጥቶ አሽከርካሪው መንጃ ፈቃዱ ለ3 ወር ይታገዳል፡፡ | | |
| 6 | የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ከሁለት ጊዜ በላይ መጣል ወይም ማበላሸት | 1,000.- ብር ተቀጥቶ ክፍያውንም ጭምር በመክፈል ፈቃዱን እንደ አዲስ እንዲያወጣ ይደረጋል፡፡ | | |

## 17. የቅሬታ አቀራረብ

17.1. በአንቀጽ 16 (ሀ-ሰ) እና በተገለፀው የቅጣት ሰንጠረዥ መሠረት ቅጣት የተላለፈበት እና በተላለፈበት ቅጣት ተገቢነት ላይ ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ሰው፡-

ሀ. በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኤጀንሲው በፅሁፍ ለማቅረብ ይችላል፤

ለ. ኤጀንሲው የቀረበለትን ቅሬታ ቅሬታው በቀረበለት ሦስት ቀናት ውስጥ መርምሮ ምላሽ መስጠት አለበት፤

ሐ. በኤጀንሲው ውሳኔ ተገቢነት ላይ ቅሬታ ያደረበት ወይም ኤጀንሲው በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ኤጀንሲው ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ወይም ውሳኔ መስጠት ከነበረበት ቀን አንስቶ በሦስት የሥራ ቀናት ቅሬታውን ለቢሮ ለማቅረብ ይችላል፡፡

17.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (17.1) በተደነገገው መሠረት ቅሬታውን አቅርቦ ቅጣቱን ካላሻረ በስተቀር የተጣለበትን ቅጣት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡

17.3. ቅጣቱን በአስር የሥራ ቀናት ያልከፈለ ሰው ከ11ኛው ቀን ጀምሮ በየቀኑ ከዋናው ቅጣት 5 በመቶ ተጨማሪ እየተሰላ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሰድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የሚመለከተው አካል ይህ መመሪያ በአግባቡ እንዲፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 19. ስለተጠያቂነት

ይህን መመሪያ የሚያስፈፅም ማንኛውም ሰው በሚያከናውናቸው ተግባራት የተሰጠውን ሃላፊነት ተላልፎ ቢገኝ የሚወሰድበት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ህግም ሊጠየቅ ይችላል፡፡

### 20. የተሻሩ መመሪያዎች

20.1. በደብዳቤ ቁጥር 818/አ.210/1 በቀን 11/8/04 ስለከባድ የጭነት ተሽከርካሪ መንቀሳቀሻ ፈቃድ አሰጣጥ የተላለፈው ሰርኩላር በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

20.2. በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረግ የከባድ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን በህዳር ወር 1996 የወጣው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

20.3. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት፣ ማሽነሪዎችን እና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2011 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

### 21. መመሪያዉን ማሻሻል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድ እና ትራንስፖርት ቢሮ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል፡፡

### 22. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 30 ቀን 2011 ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡


አዲስ አበባ

ሰኔ 30 ቀን 2011ዓ.ም.

ሰለሞን ኪዳኔ ዘነየ (ፒኤች.ዲ.)

የአዲስ አበባ ከተማ ኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪና

የትራንስፖርት ቢሮ ሀላፊ




ስዕል 1፡ የመንቀሳቀሻ ፍቃድ ንድፍ።